# በአትላንታ ጆርጂያ
# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ
# ሰዓሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም
# ካቴድራል፤

# የአሰተዳደር ፣ የፋይናንስና የንብረት
# የውስጥ መመሪያ

**ጥቅምት ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም**
(October 30, 1995) **ለመጀመሪያ ጊዜ ተዘጋጀ**

**መስከረም ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም**
(September 18, 2005) **ለሁለተኛ ጊዜ ተሻሻለ**

**ጥር ፲፫ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም**
(January 21, 2012) **ለሦስተኛ ጊዜ ተሻሻለ**

## ዓላማ

ይህ የውስጥ መመሪያ በአትላንታ ጆርጂያ የሰዓሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተገለፁት አበይት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው በአፈፃፀም ረገድ፤

1. ምዕመናን በቤተክርስቲያኗ በአባልነት ተመዝግበው የሚሳተፉባቸውን ሁኔታዎች እና በቤተክርስቲያኗ አስተዳደር ጋርም የሚኖራቸውን ግንኙነት ከደንቡ ጋር በተጣጣመ መንገድ አንድ ዓይንትና የማያሻማ ለማድረግ፤

2. የቤተክርስቲያኗ ገንዘብ እና ንብረት ከሚገኝበት ምንጭ ጀምሮ ተሰብስቦ፤ ተመዝግቦ፤ ታውቆ እና ተቀምጦ በአግባቡ ሥራ ላይ የሚውልበትን መንገድ አንድ ወጥ ሆኖ እንዲሰራበት ለማድረግ፤

3. ለተወሰነ የአገልግሎት ዘመን ከምዕመናኑ መካከል ተመርጠው በጋራ  አመራርና በግል ሀላፊነት ተመድበው የሚሰሩ የቦርዲም ሆነ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላት የተመደቡበትን ሥራ በሚመለከት ከምዕመናኑ የሚቀርቡ ጉዳዮች በማስተናገድም ሆነ በየደረጃው ካሉ አካላት ጋር በመገናኘት የሚከናውነትን ተግባር በሚመለከት መንደርደሪያ ፎርማት እንዲኖራቸው ለማስቻል፤ እና

4. በደንቡ ለይ በተለያዩ ቦታዎችና ጠቅለል ባለ አገላለፅ የተጠቀሱትን ፋይናንስና ንብረት ነክ ጉዳዮች አንድ ላይ በዝርዝር አሰቀምጦ ከእንቅስቃሴው ጋር የቀረበ ግንኙነት የሚኖራቸው አካላት ሁሉ ተመሳሳይ ግንዛቤ ሊጨብጡ የሚችሉበትን መንገድ ለመቀየስ እንዲረደ ታሰቦ የተዘጋጀ ነው፤

የውስጥ መመሪያው በማህበረ ምዕመናን ጉባኤ የፀደቁ አበይት ነጥቦችን ሳይለውጥ አፈፃፀሙ በቦርድ እየተገመገመ እንደወቅቱ ተጨባጭ ሀኔታ እና እንደቤተክርስትያኗ የፋይናንስ አቅም የእድገት ደረጃ በሙሉም ሆነ በከፊል የሚሻሻል ይሆናል፤ ለዚህ የውስጥ መመሪያ ይዘት እንዲያመች በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተበታትነው የተገለፁት ፋይናንስና ንብረት ነክ ጉዳዮች ሰብስብ ተደርገው በአንድ ገፅታ ሲታዩ...
ቤተክርስቲያኗ በስሟ ተመዝግቦ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ፤ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ልዩ ልዩ ንብረቶች እንደሚኖራት፤ መንፈሳዊ አገልግሎቷንም በቋሚ አባልነት ለተመዘገቡ ብቻ ሳይሆን በኦርቶዶክስ ክርስቲያንነታቸው የቤተክርስቲያኗን አገልግሎት ፈልገው ለሚመጡ ጭምር እንደምትሰጥ ያሳያል፤

ይህም ስለሆነ የውስጥ ደንቡ የመተዳደሪያዋ ነዋይ ከየት ይገኛል፤ እንዴት ይሰበሰባል፤ የተስ ይቀመጣል፤ በምን መልክ ለአገልግሎት ይውላል የሚለውንና አባለትም ሆነ አባል ላልሆኑ ምዕመናን የምትሰጣቸውን የአገልግሎት አይነቶች ሊሚሉ ከሚገባቸው ሁኔታዎች ጋራ አካቶ እንዲይዝ ተደርጓል፤

ይህ ዛሬ እየተሰራበት ያለው የውስጥ መመሪያ መተዳደሪያ ደንቡን ተመርኩዞ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲወጣም ሆነ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሻሻል ያተኮረባቸው ዋና ዋና ነጥቦች እዚህ ቢያደርሱንም ዛሬ ቤተክርስቲያናችን የደረሰችበትን የእድገት ደረጃ የሌሎችንምን አፈጻጸም ማካተት አስፈልጓል።

ሀ) ወደኋላ መለስ ብለን ስናየው ያለንበት አህጉር ማለትም ሰሜን አሜሪካ በአንድ ሀገር ስብከት ብቻ መዋቀሩ በእድገት ተለውጦ በቅርብ ርቀት ሆነው የተወሰኑ ስቴቶችንና በውስጣቸው የተቀቀሙትን ቤተክርስቲያናት በመንፈሳዊ ረገድ የሚመሩ የሀገረ ስብከት ሊቀጳጳሳት በየቦታው የተመደቡበት ወቅት ላይ በመድረሳችን ፣የካቴድራላችን አስተዳደር ከሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤትም ሆነ ይህን ግዙፍ ኃላፊነት ከተቀበሉ የሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ በሁለንተናዊ መልኩ ስለሚኖረው ግንኙነት ዘርዘር ያለ መመሪያ በማስፈለጉ

ለ) በሕንጻም ረገድ በውጭው ዓለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች መሠረት አውጥተው ካስገነባቸው ሕንጻ ቤተክርስቲያናት በትልቅነቱ፣በዓይነቱም ሆነ ይዞቱ ልዩ የተባለ ሕንጻ ባለቤቶች በመሆናችን ለየት ያለ የአስተዳደርና የአጠቃቀም ሥርዓት ሊነደፍ ስለሚገባው

ሐ)በአገልጋይ ካህናትም ቁጥር ሆነ በሚሰጠው የአገልግሎት ዓይነት እና አገልግሎትም የሚሰጥባቸው ቀናት እስከዛሬ ከተመደቡት የሰንበት ቀናትና ታላላቅ በዓላት በተጨማሪ በሳምንቱ ውስጥ ባሉ ቀናት ጭምር እንዲሆኑ የምዕመናን ጥያቄ በመምጣቱ አገልግሎቶችን ዘርዘር አድርጎ ማስቀመጥና አንድ ወጥ ግንዛቤ የተከተለ ሥርዓት እንዲኖረው ማድረግ ወቅቱ የጠየቀው ጉዳይ በመሆኑ

መ)ምዕመናንም በተለያዩ መልኮች እየተሳሰቡ በቤተክርስቲያቸው ዙሪያ ትውልድን ለመተካት፣ ማህበራዊ ሁኔታዎችን ለማዳበር፣በጋራ የሚደረጉ ጉልህ ተግባራትን ለመቀላጠፍ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ በየዘመኑ የሚመረጠው አስተዳደር ወጥነት ያለው መንደሪደርያ ተከትሎ ለማስተባበርም ሆነ ፈጣንና ቀልጣፋ ድጋፍ ለመስጠት እንዲችል መንደርደሪያ የሚሆኑ አንዳንድ ነጥቦች ለማሳየት እንዲቻለው፣

ይህ የቤተክርስቲያናችን <u>የአስተዳደር</u> ፣<u>የፋይናንስና</u> <u>የንብረት</u> አያያዝ <u>የውስጥ መመሪያ</u> <u>ለ3ኛ</u> ጊዜ እንዲሻሻል ተደርጓል።

# 1. <u>የገቢ ምንጭ</u>

ይህ የውስጥ ደንብ መመሪያ በተሻሻለበት ወቅት የሚታወቁትና <u>የቤተክርስቲያኗ ገቢ</u> የሚባሉት፤

1.1 እያንዳንዱ አባል በተወሰነ ጊዜ የሚከፍለው የአባልነት መዋጮ፤

1.2 ቤተክርስቲያኗ ለምትሰጠው ልዩ አገልግሎት የሚደረገው ክፍያ፤

1.3 በሰንበትና በበአላት ከምዕመናን የሚሰበሰበው ሙዳየ መፅዋእት፤

1.4 በማንኛውም መልኩ የሚገባ የስእለት ገንዘብ፤

1.5 ምዕመናን በራሳቸው ፈቃድና ውሳኔ ከገቢያቸው አስልተው ለእግዚአብሔር ቤት ከሚከፈሉት አስራት የሚሰበሰብ፤

1.6 ለገቢ ማጎልበቻ ታስበው ከሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች የሚገኝ ገቢ ማለትም ከሰንበት ምሳ፤ ከልዩ ልዩ የበአል ዝግጅት እንዲሁም ጧፍ፤ እጣን፤ ሻማ፤ ጃንጥላ፤ የመዝሙር ካሴት፤ ካሌንደርና ልዩ ልዩ ኦርቶዶክሳዊ የሆኑ የቤተክርስቲያናትን እንቅስቃሴ የሚያሳዩ ቪዲዮ ካሴቶች ዲቪዲዮች እና ከመሳሰሉት ሽያጮች የሚገኙ ገቢዎች

1.7 የቤተክርስቲያኗን ልዩ ልዩ ክፍሎችም ሆነ የመገልገያ ቁሳቁሾች በማከራየት የሚገኝ ገቢ

1.8 የካቴድራሉን የሞርጌጅ እዳ ለመቀነስና በአጭር ጊዜም ከፍሎ ለመጨረስ፣ሲባል በተለያዩ አቀራረቦች ምእመናን ለተወሰነ ጊዜ ቃል ገብተው ከሚያስገቧቸው ችሮታዎች ሁሉ ናቸው።

# <u>2.ንብረት</u>

ይህ የውስጥ መመሪያ በተዘጋጀበት ወቅት የሚታወቁትና <u>የቤተክርስቲያኗ ንብረት</u> የሚባሉት ደግም፤

2.1 የቤተክርስቲያኗ ሕንፃና ተያይዘውም የሚገኙ መገልገያ ቤቶች ከነ ቅጥር ግቢው፤

*1152 South Stone Mountain Lithonia Rd Lithonia , GA 30058*

2.2 በቤተመቅደሱና በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የሚገኙ ንዋየ ቅድሳት፤

2.3 በማናቸውም መልክ ለቤተክርስቲያኗ መንፈሳዊም ሆነ ማኅበራዊ መገልገያ እንዲሆን የተገዙ ወይም በስጦታ የተገኙ በቤተክርስቲያኗ ውስጥም ሆነ ተያይዘው በሚገኙ ቤቶች እንዲሁም <u>የቤተክርስቲያኗ ንብረት</u> ተብለው የተመዘገቡ አድራሻዎች ውስጥ የሚገኙ ቋሚነት ያላቸው ቁሳቁሶች ሁሉ ናቸው፤

2.4 <u>ተጨማሪ</u>

በ (266 Robin St. Decatur, GA. )

የሚገኙ ቤቶች ሁሉ የቤተክርስቲያኗ ንብረት ናቸው።

# 3. የገንዘብና ንብረት አያይዝ

## አጠቃላይ መርህ

3.1 የቤተክርስቲያኗ ማንኛቸውም አይንት ንብረት የሀገሪቱ ሕግና ደንብ በሚፈቅደው መሰረት በአግባቡ በዘመናዊ የንብረት ዘዴ በሕጋዊና አስተማማኝ ቦታዎች ይቀመጣል፤

3.2 በማንኛቸውም መልክ በቤተክርስቲያኗ ስም የሚሰበሰብ ገንዘብ ሁሉ በቤተክርስቲያኗ ሰም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ብቻ ይቀመጣል፤

3.3 የቤተክርስቲያኗ ማንኛውም ገንዘብም ሆነ ንብረት ለቤተክርስቲያኗ አገልግሎት ብቻ ይውላል፤

3.4 ማንኛውም የቤተክርስቲያኗ ክፍያዎች በም/ሊቀመንበሩና በገንዘብ ያዡ ጥምር ፊርማ በቼክ ብቻ ይፈጸማል።

# 4. "ንብረት" ግኝቱና አያይዙ

በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ እንደተገለፀው የቤተክርስቲያኗ ንብረቶች የሚንቀሳቀስ፤ የማይንቀሳቀስ፤ ቋሚ፤ እና አላቂ ንዋየ ቅድሳትና፤ ሌሎች ቁሳቁሶች ተብለው ይመዘገባሉ፤

4.1 የቤተክርስቲያኗ ቋሚ ንብረቶች በሙሉ ከዝርዝር ማብራርያ ጋር ተመዝግበው ተከታታይ ቁጥር እንዲኖራቸውና በሚመች ቦታ እንዲለጠፍባቸው ተደርጎ በንብረት ሹሙ የቅርብ ቁጥጥር ስር መቀመጥ አለባቸው፤

4.2 ቋሚ ንብረቶች ተብለው ቁጥር የሚሰጣቸው በግዢም ሆነ በሰጦታ ተገኝተው ለቤተክርስቲያኗ አገልግሎት እንዲውሉ የተመደቡት ሲሆኑ ለምሥጢራተ ቤተክርሰትያንና ለሌሎች መንፈሳዊ አገልግሎቶች የሚውሉት በሙሉ በደብሩ አሰተዳዳሪ ካህን ወይም በሚመድቡት የቤተክህነት ሰው ኃላፊነት ስር ለአገልግሎት ይውላሉ፤ ለነዚህም አይነት ንብረቶች ልዩ ግምጃ ቤት ተደራጅቷል፣

4.3 አላቂ ነው ተብሎ የሚገመት እቃ ሁሉ በዚሁ ርእስ ተመዝግቦ ለአገግሎት በሚውልበት ግዜ እየተመዘገበ ወጭ እንዲደረግ ያሰፈልግል፤ ከዚህ መካከል ለሽያጭ የሚደረግ ካለ ደግም በዚህ የውስጥ ደንብ ም.1 ቁ. 12. መሰረት መፈፀም አለበት፤

4.4 በመተዳደሪያ ደንቡም ሆነ በዚህም የውስጥ ደንብ መሰረት የተዘጋጀና ወደፊትም የሚዘጋጅ የንብረት ዝርዝር አንድ ኮፒ ለቁጥጥር ኮሚቴው መድረስ ይኖርበታል፤ በየግዜው የንብረት ቆጠራ ሲደረግም የዘገባው ኮፒ ለዚሁ አካል መድረስ ይኖርበታል፤

*4.5 በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ለቤተክርስቲያኗ የተደረገና የሚደረግ ስጦታ ሁሉ ፍጹም የቤተክርስቲያኗ ንብረት ነው በሚለው መሠረት የግለሰብ ወይም የቡድን ወይም የሌላ አካል ከገቢው የተወሰነ ድርሻ ወይም የሽያጩ ከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚጠይቅበትን ማንኛውም ዕቃ በዚሁ አንቀጽ ስር ባሉት ተከታታይ ቁጥሮች ስር በተለይ ከተገለጹት ሁኔታዎች በስተቀር አትረከብም።*

*4.5.1 ስምዕመናን መንፈሳዊ እውቀትና ጠቀሜታ እንዲሰጡ ታስበው መዘጋጀታቸው፣በማያሻማ የሚገልጽ እቃዎች ከሆኑ ናሙናውን ብቻ በመገምገም ጠቃሚነታቸው በሚመለከታቸው አካላት ሲረጋገጥ ይህ ማለትም ስለነገረ መለኮት ይዘታቸውና የቤተክርስቲናችንን ትምህርትና ቀኖና ስለመከተላቸው በደብሩ አለቃ ካህንና በስብከተ ወንጌል መምሪያው (መምህሩ)ኃላፊ በጹሑፍ ፣*

*-ብምእመናን መካከል ተሸጠው ለቤተክርስቲያኗ የማይናቅ ገቢ ያስገኛሉ ወይም ለአባላት በነጻም ቢሆን ቢታደሉ ስነልቦናዊ ጠቀሜታ አላቸው የሚባሉ ከሆኑ ደግሞ በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ታምኖበትና ብዛቱም ሆነ ዋጋው ተወስኖ በጹሁፍ ማረጋገጫ ሲደገፍ ብቻ በዱቤ ሰነድም ሆነ እጅ በእጅ በሆነ ክፍያ ገዝታ ልትረከብ ትችላለች።*

## 5. <u>“ገንዘብ” ግኝቱ አሰባሰቡና አያያዙ</u>

<u>አጠቃላይ</u>

**በተለያዩ ርእሶች እንደተገለፀው ቤተክርስቲያኗን በአስፈላጊው ሁሉ መደገፍ፤ መርዳት፤ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የሆነ ክርስቲያን ሁሉ ኃላፊነት ነው ቢባልም ቤተክርስቲያኗ አገልግሎቷን ሳታቋርጥ እንድትቀጥል ለማድረግ ቢያንስ ቢያንስ የማይቀሩ ናቸው የሚባሉትን ወጭዎች የሚሸፍን ገቢ ከሚያስተማምን ምንጭ በማያቋርጥ መልክ የሚገኝበትን መንገድ መፈለግ የግድ ይሆናል፤የእምነቱ ተከታዮች ቤተክርስቲያኗን የሚረዱበት መንገድ ብዙ ሊሆን ይችላል ተብሎ ቢገመትም ባንድ ወጥነት ሁሉንም ሊያሳትፍ የሚችል ያስተዋፅኦ አይነት <u>በነፍስ ወከፍ የተመጠነ</u>፤ <u>በጊዜ የተሰላ</u>፤ <u>በፍላጎት ላይ የተመረኮዘ</u>፤ <u>የውዴታ ግዴታ ያለበት</u>፤ አንድ አይነት መዋጮ ሲኖር ብቻ ነው፤ ይህንንም ማድረግ የሚችሉት አባላት ብቻ ናቸው፤**

## 5.1 <u>የአባላት መዋጮ</u>

**ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳት የቤተክርስቲያኗ የአባልነት ክፍያ እንደሚከተለው ተወስኗል፤**

<u>5.1.1 **እንደሚከተለው ተሻሻሏል**</u>

**- አንድ ለብቻው የሚመዘገብ አባል በዓመት** $150.00 **ብር ይከፍላሉ፤**

**- ባልና ሚስት የሆኑ አባላት በዓመት**$240.00 **ብር ሲከፍሉ፤**

**- ክፍያውንም ቢቻል በአንድ ጊዜ አለበለዚያም በስሌት** 2 **ጊዜ።**

**እንዲከፍሉ ሲወሰን ላስተዳደርና ለፋይናንስ ቁጥጥር እንዲያመች ደግም የአባልነት ክፍያ**
**በዓመቱ መጀመሪያ ወር (January) እና በ (July) እንዲሰበሰብ በጉባኤ ሰምምነት ተደርጎበታል።**

5.1.2 **እያንዳንዱ አዲስም ሆነ መደበኛ አባል ለሚከፈለው የአባልነት መዋጮ በአርእስቱ የተመዘገበ ደረሰኝ ይሰጠዋል፤**

(**ናሙና ቅፅ** 1 **ይመልከቱ**)

5.1.3 **እያዳንዱ አባል ለሚከፈለው መዋጮ ከሚሰጠው ህጋዊ ደረሰኝ ሌላ በቤተክርስቲያኗ ስምና አርማ የተዘጋጀ መለያ ቁጥርና የአባሉ ሙሉ ስም የአለበት**

የ "አባልነት መታወቂያ ካርድ" ተዘጋጅቶ ይሰጣዋል፤

(ናሙና ቅጽ 9 ይመልከቱ)

# 6. ሙዳዬ ምፅዋት

ሙዳዬ ምፅዋት የሚባለው በመደበኛው የሰንበት ዕለትና የተለየ በአል በሚከበርበት ዕለት ምዕመናን እንደችሮታቸው የሚሰጡት ምፅዋት ለመቀበል በአማካይ ቦታ ከሚቀመጥ ወይም የተወከሉ የቤተክርስትያኑ አገልጋዮች በሕዝቡ መካከል አዙረው ከሚሰበሰቡበት ዕቃ ውስጥ የሚቆጠር የቤተክርስትያኗ ገቢ ማለት ነው፤

በዚህ ሁኔታ የሚገኘው ገንዘብ አያያዝም በዚህ የውስጥ ደንብ እንደሚከተለው እንዲፈጸም ተወስኗል፤

6.1 በመደበኛ የሰንበት ዕለትም ሆነ በልዩ የበአል ቀን ሙዳየ መፅዋት የሚሰበስቡ ግለሰቦች በቅድሚያ በሥራ አሰኪያጅ ኮሚቴው የተመደቡ ብቻ ናቸው፤ የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በሰተቀር የሙዳዬ መፅዋት መሰብሰቢያ የሚዞረው በተመራጮች መሆን አለበት፤

6.2 በማንኛቸውም ጊዜ በሙዳየ መፅዋት መልክ የተሰበሰበውን ገንዘብ በዚያኑ ጊዜና ሰዓት ገንዘብ ያዡውን ጨምሮ ሦሰት አባላት በጋራ ቆጥረው ለዚሁ ማረጋገጫ በተዘጋጀው የዕለተ ሰንበት ልዩ ልዩ ገቢዎች <u>ማጠናቀሪያ</u> ቅፅ ላይ ሦሰቱም ይፈርማሉ በተከታዩ የስራ ቀንም በለሎች አርእሰቶች ከተገኙ ገቢዎች ጋር ተደምሮ ባንክ ገቢ መደረግ አለበት፤

( ናሙና ቅፅ 3 ይመልከቱ)

6.3 በቋሚነት በቤተክርስቲያኗ ውስጥ የሚኖረው የሙዳየ ምፅዋት መስብሰቢያ ሣጥን በወር አንድ ጊዜ፤ በወሩ መጨረሻ በሚውለው እሁድ ዕለት ከላይ በተራ ቁጥር 6.2 የተጠቀሱት አባላት ባሉበት ተከፍቶ ይቆጠርና ከዕለቱ ልዩ ልዩ ገቢዎች ጋር ተመዝግቦ ባንክ ገቢ ይደረጋል፤

# 7. የስዕለት ገንዘብ

ስዕለት ማለት ሰው ወዶ እራሱ ለእግዚአብሔር የሚገባው ቃል ኪዳንና እሱም ከእግዚአብሔር የሚያገኘው በረከት ማለት ነው፤ ስለዚህ ሰዕለታቸውን ለማድረስ የሚፈልጉ ምዕመናን እንደፍላጎታቸው በአይነት ወይም በገንዘብ ሊያደርጉ ይችላሉ፤
የዚህ ገለፃ አላማ የሰዕለትን መንፈሳዊ ይዘት ለማብራራት ወይም ለመገደብ ሳይሆን ከገንዘብና ከንብረት ጋር የሚያያዙ ጉዳዮችን አፈፃፀም ፈር ለማስያዝ ስለሆነ፤

7.1 ምዕመናን በሰዕለት መልክ ለቤተክርስቲያኗ በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ የሚያስገቡት ገንዘብ መጠኑ ተረጋግጦ ለገንዘብ ተቀባዩ ቆጥሮ ሊቀበለው በሚችል መልኩ ከተሰጠ እንደማንኛቸውም ገቢ በአርእስቱ ተመዝግቦ ለሰጭው ምዕመን ደረሰኝ ይቆረጥለታል፤

7.2 የሰዕለት አስገቢው ምርጫ ሰዕለቱን በቤተክርስቲያኑ ውስጥ በተቀመጠው የገንዘብ መሰብሰቢያ ሳጥኖች ውስጥ ማስገባት ከሆነ ይችላል፤ በዚህም መልክ የሚገባ ገንዘብ ከመሰብሰቢያው ሳጥን ተከፍቶ በሚቆጠርበት ጊዜ በዚህ ውስጠ ደንብ ም.1 ቁ. 6.2/6.3 በተወሰነው መሰረት ከሚመዝገብና ገቢ ከሚሆን በሰተቀር ለግስሰቦች የግል ደረሰኝ አይቆረጥም፤

## 8. አሥራት

አሥራት ማለት ማንኛውም ሰው እግዚአብሔር ከሰጠው ሃብትና በረከት በራሱ ስሜትና ፍላጎት ተነሳስቶ ገቢውን በማስላት አሥር ከመቶ ለቤተክርስቲያን የሚለግሰው ገንዘብ ነው፤ ምዕመናን በአሥራት መልክ ለቤተክርስቲያን የሚያደርጉትት መዋጮ በሚገባ ታውቆና ተመዝግቦ ሊያዝ ስለሚገባውና ለከፋዮቹም ህጋዊ ማስረጃ ሊሰጣቸው ስለሚያስፈልግ አሥራት ከፋዮች ስማቸውንና የከፈሉትን መጠን ሞልተው በማሸግ ሳጥን ውስጥ እንዲጨምሩ የሚያገለግል ልዩ ኢንቨሎፕ ተዘጋጅቶ በ "አሥራት መሰብበቢያ ሳጥን" ላይ ይቀመጣል፤

8.1 በዚህም መልክ የሚገኝ ገቢ በእያንዳንዱ ከፋይ ስም ተመዝግቦ ይያዛል፤
8.2 እያንዳንዱ ከፋይም በሰሙ ደረሰኝ ተቆርጦ ይሰጠዋል፤

## 9. የአገልግሎት ክፍያ

ቤተክርስቲያኗ በምዕመናን የተቋቋመችና በምዕመናን ተደግፋ ለምዕመናን አገልገሎት የምትሰጥ እንደመሆኗ ከመደበኛ ፀሎትና ቅዳሴ ውጭ በተጨማሪ ለምትሰጠው ልዩ አገልግሎት መጠነኛ ክፍያ ብታስከፍል ተገቢ መሆኑ ታምኖበት አንድ ወጥ አይሁን እንጅ እስከዛሬ ሲሰራበት ቆይቷል፤

በምዕመናን ዘንድ በውል እንደሚታወቀው በእያንዳንዳችን ላይ የሚደርሱትን የቤተክርስቲያንን አግልግሎት የሚጠይቁ ጉዳዮች፤ የተወሰኑት፤ አስቀድመሙ ታውቀው በእቅድ የሚከናወኑ (ለምሳሌ፤እንደቀለበት፤ ተክሊል፤ ወዘተ.)
አንዳንዶች ደግሞ፤ ረዘም ካለ ጊዜ በፊት ሊታሰብባቸው የሚቻል (ለምሳሌ፤ እንደክርስትና፤ የሙት አመት መታሰቢያ ወዘተ.) ለሎች ደገሞ፤ በድንገት የሚደርሱ ሁኔታዎች (ለምሳሌ የሞት አደጋ ደርሶ የትኩስ ሬሳ ፍታት) እና የመሳሰሉት ናቸው፤

የአባላት ቁጥር በርክቶ ቤተክርሰቲያኗን ያለችግር ለማንቀሳቀስ የሚያሰችል አሰተማማኝ ገቢ በአባልነት ቋሚ መዋጮም ሆነ ከሌሎቸ ርእሶች መገኘቱ ሲረጋገጥ አባላት ከቤተክርሰቲያኗ ለሚጠይቁት ልዩ አገልግሎት ምንም ተጨማሪ ክፍያ የማይከፍሉበት ጊዜ ወደፊት እንደሚመጣ ቢታወቅም የአሁኑ አቅማችን አባላትን ከክፍያ ነፃ ለማድረግ አላሰቻለንም፤ ይህ ሁኔታ በየወቅቱ በቦርዱ እየተገመገመ ከዛሬው ስሌት ዝቅ ወደአለ፤ ብሎም ጨርሶ ነፃ ወደሚሆንበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፤

ከላይ የተገለፀውን ጉዳዮች በሚመለከት እንደ ጉዳዮቹ አይነትና ቤተክርስቲያኗም እንደምትሰጠው የአገልግሎት ደረጃ የሚለያዩ ሆኖ አገልግሎቱን የጠየቁ ወገኖች ከዚህ በታች በተዘረዘረው መጠን እንዲከፈሉ ተወስኗል፤
በካህናት ቁጥርም ሆነ በገነባነው ህንጻ የተማላ መሆን እንዲሁም ለተገልጋይ ምዕመናን ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ወቅቱ የፈቀደውንና በአቅም ደረጃም ማድረግ የሚቻለውን ለማድረግ ሲባል ካህናትና አስተዳደሩ በጋራ አጥንተው የተስማሙበት የአገልግሎት ኣይነትና አፈጻጸሙም በዚህ በተሻሻለው የውስጥ መመሪያችን ውስጥ በሰፊው እንዲካተት ተደርጓል።

ይህ የውስጥ መመሪያ ለ3ኛ ጊዜ በሚሻሻልበት ወቅት ቀጥሎ በሰፊው የተዘረዘሩት የአገልግሎት ዓይነቶች በአዘቦቱም ቀናት እንዲከናወኑ ስታቀድ ይህ ትልቅ ሕንጻ አዘውትሮ ለአገልግሎት

ሊከፈት ለእንክብካቤውና ጥበቃው የሚጠይቀውን ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን፣አገልጋይ ካህናትም ቢሆኑ በነዚህ ዕለት ሰንበት ከሚሰጡት ያልተቆጠበ አገልግሎት ላይ እየታሰበ ሊዶጎሙበት እንደሚገባ ከወዲሁ ታስቦበት በነዚህ ክፍያ በሚጠየቅባቸው ቀናት ልዩ አገልግሎት የሰጡ ካህናት የገቢውን 80% እንዲካፈሉት ተወስኗ።ይህም በሥርዓት ይፈጸም ዘንድ ለአገልግሎቱ የሚያስፈልጉትን አገልጋዮች ብዛት የደብሩ አለቃ እየወሰኑ ይመድባሉ።

**<u>በአትላንታ ሰዓሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ካቴድራል ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች</u>**

1) ሥርዓተ ቅዳሴና የወንጌል ስብከት አገልግሎት

2) ኦርቶዶክሳዊ ሥርዓተ ጥምቀት

3) ኦርቶዶክሳዊ ሥርዓተ ቀለበት

4) ኦርቶዶክሳዊ ሥርዓተ ጋብቻ

5) ፀሎተ ፍትሐት ለሙታን ማከናወን

6) ምዕመናን ለቅዱስ ቁርባን ማዘጋጀት

7) በአልጋ ቁራኛ ያሉትን ሕሙማን መጎብኘት

8) በሐዘን ላይ ያሉትን ማጽናናት

9) የምክርና የማስታረቅ አገልግሎት ለምዕመናን መስጠት

ከላይ የተዘረዘሩት ልዩ ልዩ አገልግሎቶች በቤተክርስቲያናችን የሚከናወኑ ሲሆን አፈጻጸማቸው ከዚህ እንደሚቀጥለው ይሆናል።

### 1) <u>*ሥርዓተ ቅዳሴና የወንጌል ስብከት አገልግሎት*</u>

በመደበኛው ቀን በየሳምንቱ እሁድ የሚሰጥ ሲሆን በተጨማሪ በሚከተሉት ዕለታት ይከናወናል፣

ሀ) በየወሩ የማርያም ዕለት

ለሕዳር ጽዮን (ክብረ በዓል)

የጥር ማርያም አስተርዮ

ለ) ዓመታዊ የመድሃኒዓለም ዕለት
የጥቅምት መዳህኒዓለም

የመጋቢት መደህኒዓለም (ክብረ በዓል)

ሐ) ዓመታዊ የቅዱስ ሚካኤል እለት
የህዳር ሚካኤል (ክብረ በዓል)

የጥር ሚካኤል

የሰኔ ሚካኤል (ክብረ በዓል)

መ) ለፍልሰታ ማርያም

16ቱን ቀን ለፍልሰታ ማርያም

በየእለቱ የውዳሴ ማርያም ትርጉምና ኪዳን፦ የሰርክ ጸሎት አገልግሎት ይካሄዳል

ሠ) በአቢይ ጾም በየእለቱ ኪዳንና የሰርክ ጸሎት አገልግሎት ይሰጣል።

ረ) ምዕመናን በአዘቦቱ ቀን እንዲቀደስላቸው ከጠየቁ የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ሊያስቀድሱ ይችላሉ።

የክፍያው መጠን፦ ለአባል - $450 አባል ላልሆነ $500

## የወንጌል ስብከት

ከመደበኛው ቅዳሴ ጋር ከሚሰጠው ትምህርት በተጨማሪ፣

ሀ) በዓመት ሁለት ጊዜ የወንጌል ጉባኤ
ለሕዳር ጽዮን እና በአቢይ ጾም

ለ) በየሳምንቱ እሁድ በሬዲዮ ስርጭት

ሐ) የረቡዕ ማታ (ቤተክርስቲያን/በቴሌኮንፍራንስ) ትምህርት

መ) የወጣቶች ዓመታዊ ሴሚናር

## 2) ኦርቶዶክሳዊ ሥርዓተ ጥምቀት (ክርስትና)

የቤተክርስቲያናችን አንዱ ትልቁ አገልግሎት በዚህ በስደት ያለነውን አማኞች ልጆች በዕምነታችን መሰረት ወንዶች በ40 ቀን ሴቶች በ80 ቀን ማጥመቅ ሲሆን ለዚሁ አገልግሎት የሚገባውን መመሪያ አዘጋጅቶ ይህ አገልግሎት እንዲከናወንላቸው ለሚጠይቁ ሁሉ በቅድሚያ እንዲደርሳቸው ማድረጉ ሊያውቁት የሚገባቸውን እንዲያውቁና እንዲመሩበት ለረዳቸው ይችላል።

በመደበኛው የአገልግሎት ቀን (እሁድ) ክርስትና ለሚያስነሱ ምዕመናን የአገልግሎት ክፍያው እንደሚቀጥለው ይሆናል።

| | |
|---|---|
| አባል ለሆኑ | በነጻ |
| አባል ላልሆኑ | $100 ሲሆን የምስክር ወረቀት ማዘጋጃ $10 |

ክርስትናው በሚፈልጉት ቀን ማለትም ከመደበኛው ቀን ሌላ ከሆነ የአገልግሎት ክፍያው

አባል ለሆኑ $450 ብር - አባል ላልሆኑ $500 ብር ይሆናል።

## 3) ኦርቶዶክሳዊ ሥርዓተ ቀለበት

ሥርዓተ ቀለበት ከቅዱስ ቁርባን ጋብቻ በፊት የሚፈም የቃልኪዳን ሥነሥርዓት ሲሆን አፈጻጸሙ እንዴት መከናወን ይኖርበታል፣

ሀ) ሥርዓተ ቀለበቱ እንዲከናወንላቸው ለሚጠይቁ ኦርቶዶክሳውያን በቤተክርስትያናችን ደንብና ሥነስርአት መሰረት ምክርና ትምህርት እንደሚያስፈልግ

ለ) የቀለበቱ ሥነስርዓት ሊፈጸም የሚችለው በቤተክርስቲያን ውስጥ ብቻ ሲሆን ያገልግሎት ክፍያው እንደሚቀጥለው ይሆናል።

| | |
|---|---|
| አባል የሆኑ | $500 ብር |
| አባል ያልሆኑ | $700 ብር ይሆናል። |

## 4) ሥርዓተ ጋብቻ

ሥርዓተ ጋብቻ በአሁኑ ጊዜ በቅዱስ ሲኖዶስ ተወስኖ በአለው ሥነ ሥርዓት መሰረት ቤተክርስቲያናችን በቅዱስ ቁርባን ብቻ መሆን እንዳለበት ተጠብቆ

ሀ) ተጋቢዎቹ (ሙሽሮቹ) የቅድመና የድሕረ ጋብቻ ምክር (ትምህርት) መቀበል እንዳለባቸው

ለ) የሠርጉ ሥነስርዓት የሚከበርበት ቀንና ሰዓት የተከበረ መሆኑን የሚያስረዳና በጋብቻ ኑሮአቸው መጠበቅ

ያለባቸውን መንፈሳዊ ህይወት ትምህርት አዘል ጽሁፍ ተዘጋጅቶ በቅድሚያ እንዲደርሳቸው ይደረጋል።

ሐ) የአገልግሎት ክፍያ __ አባል ለሆኑ __$300 አባል ላልሆኑ __$500 ብር ይሆናል።

## 4) ፀሎተ ፍትሐት

በቤተክርስቲያናችን ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የሚሰጡት የፍትሐት አገልግሎቶች

1) እግዚአህያዋን

2) በመደበኛው ቅዳሴ ላይ

3) ትኩስ አሬሳ

1) እግዚአሕያዋን የፍትሐት አገልግሎት አፈጻጸም እስከዛሬ በቤተክርስቲያናችን ውስጥ በመደበኛው የቅዳሴ ቀን ሲሆን

አሁን ግን እድገታችንንም ምክንያት በማድረግ ምዕመናን በቀኑ እንዲፈጸምላቸው ከጠየቁ የሚከተለውን የአገልግሎት ክፍያ

በመክፈል ሊፈጸምላቸው ይቻላል።

<u>በመደበኛው የቅዳሴ አገልግሎት ቀን፤</u>

በቅዳሴ ጊዜ የሚታሰብ አባል ለሆኑ - $50 ብር አባል ላልሆኑ -$100 ብር

ሙሉ ፍትሐት አባል ለሆኑ - $75 ብር አባል ላልሆኑ -$125 ብር

<u>ከመደበኛው የቅዳሴ ቀን ውጭ</u> ማለትም ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ባሉት ቀናት አገልግሎት ከተፈለg ክፍያው

አባል ለሆኑ - $450 ብር አባል ላልሆኑ -$500 ብር ይሆናል

ከዚህም ጋር ተያይዞ ካህናት በግላቸው በሀውልት ምረቃ ላይ መገኘት ይችላሉ።

ለዚህ አገልግሎት ሲጠየቅ ከተወሰነ ጊዜ በፊት አስተዳደሩና የቤተክርስቲያኑ አለቃ በቅድሚያ ማወቅ ሲገባቸው

የቤተክርስቲያኑም አለቃ እንዲሁ ለካህናቱ በቅድሚያ እንዲያውቁት ማድረግ ይኖርባቸወል፤

2) በመደበኛው ቅዳሴ ላይ ለሚደረገው የፍትሐት አገልግሎት ከተወሰነ ሰምንት በፊት መታወቅ አለበት።

3) ለትኩስ አሬሳ የሚሰጠው የፀሎተ ፍትሐት አገልግሎት የሰው ልጅ የሚጠራበትን ቀን ስለማያውቀው በአዘቦቱም ቀን

ቢሆን ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን እስከሆነ ድረስ አባልም ሆኑ አልሆኑ አገልግሎቱን እስከጠየቁ ድረስ ይፈጸምላቸወል።

ለዚህም አገልግሎት ክፍያው ለአባላት በነጻ ሲሆን አባላት ላልሆኑ ግን $300 ብር ይሆናል።

ግን በአንዳንድ ችግር ምክንያት ክርስቲያኖች ሥርአተ ጸሎቱ በ Funeral home እንዲሆን ቢጠይቁ ቤተክርስቲያኑ

በልብሰ ተክህኖ ሥርዓተ ጸሎት የምታካሂደው በቤተክርስቲያን ውስጥ ብቻ ሲሆን በምዕመናን ዘንድ ታውቆ በቤተክርስቲያን

እንዲከናወን ይመክራሉ።

## 6) ምዕመናን ለቅዱስ ቁርባን ማዘጋጀት

“ሥጋየን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው” የሚለውን የክርስቶስ ቃል ቤተክርስቲያናችን እያወጀች፣ እያስተማረች ያለ ሲሆን ይህ ትምህርት ተቀባይነት ኖሮት ምዕመናንን ለማዳን አባቶች ካህናት ጥረት በማድረግ ለቅዱስ ቁርባን በማዘጋጀት እንዲቀርቡ ማድረግ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ ያደርጋቸዋል።

7) **<u>በአልጋ ቁራኛ ያሉትን ሕሙማን መጎብኘት</u>**

ቤተክርስቲያናችን በባልጋ ቁራኛ ተይዘው የሚሰቃዩትን ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን ካህናቶቻችንም ሆኑ ምዕመናን ላልሰሙ በማሰማት በአሉበት ተገኝቶ መጎብኘትና ማጽናናት የእያንዳንዳችን ተግባር ሲሆን ይገባዋል።

8) **<u>በሐዘን ላይ ያሉትን ማጽናናት</u>**

9) **<u>የምክርና የማስታረቅ አገልግሎቶች ለምዕመናን መስጠት</u>**

# <u>የአገልግሎትና የክፍያ መጠን -ሰብሰብ ተደርጎ ሲታይ</u>

| ርዕስ | የአገልግሎት አይነት | ለአባላት | አባል ለአልሆኑ |
|---|---|---|---|
| 9.1 ክርስትና | በመደበኛ ቀን | በነጻ | $100 |
| 9.2 ክርስትና | ከመደበኛ ቀን ውጭ | $450 | $500 |
| 9.3 ቀለበት | | $500 | $700 |
| 9.4 ጋብቻ | ተክሊል | $300 | $500 |
| 9.5 ፍትሐት | በመደበኛ ቅዳሴ ላይ | $50 | $100 |
| 9.6 ፍትሐት | እግዚአህያዋን (ሙሉ ፍትሐት) | $75 | $125 |
| 9.7 ፍትሐት | ከመደበኛ ቀን ውጭ | $450 | $500 |
| 9.8 ፍትሐት | ትኩስ እሬሳ | ነጻ | $300 |

9.7 **<u>አፈፃፀም</u>**

**ከላይ የተዘረዘሩትን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ለማግኘት የሚጠይቁ ሁሉ፤**

9.7.1 **ጥያቄአቸው ቢያንስ በያንስ ከሁለት እሁድ ወይም ሁለት ሳምንት በፊት በግንባር ወይም በስልክ ለሥራ አሰኪያጅ ኮሚቴው ሊቀመንበር ወይም ፀሐፊ ያሳውቁና የቅደም ተከተል ተራ ይያዝላቸዋል፤**

9.7.2 **ለሰነድ ጥንቅር እና ለፋይናንስ ቁጥጥር እንዲረዳም የአገልግሎት መጠየቂያ ቅፅ ይሞላሉ፤ መጠይቁን የመሙላት ችግር ለሚኖርባቸው ምዕመናን ግን የሥራ አሰኪያጅ ከሚቴው ሙሉ ድጋፍ ይሰጣል፤**

**(ናሙና ቅፅ 4 ይመልከቱ)**

9.7.3 **ለሚጠይቁት አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ ሲያደርጉም በርእሱ የተመዘገበ ሕጋዊ ደረሰኝ ይሰጣቸዋል፤**

9.7.4 **ለሚጠይቁት አገልግሎት የተወሰነውን ክፍያ ለማድረግ አቅም የሌላቸው ምዕመናን ይህንኑ በራሳቸው ቃልና ፊርማ ካረጋገጡ በሥራ አሰኪያጅ ኮሚቴው ታውቆና ተወስኖ ነፃ አገልግልት ሊሰጣቸው ይችላል፤**

9.7.5 **ከድንገተኛ ትኩስ አደጋ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ከሆነ ግን ከላይ ያለው የጊዜ ገደብ ሳያግደው ችግሩ ወዲያውኑ ማሳወቅና አገልግሎቱን በጊዜው ማግኘት ይችላሉ፤**

## *10. <u>የሰንበት ምሣ</u>*

*የቤተክርስቲያኗን የፋይናንስ አቅም በማጎልመት በመሰረታዊ አስፈላጊነት የሚታወቁ ወጭዎችን ለመሸፈን አባላት በተለያየ ዘዴ ከሚያደርጉት ድጋፍ አንዱ በየሳምንቱ ቡድን ተከፋፍለው ምሳ ሰርተው በማምጣት ከቅዳሴ በኋላ ምዕመናን መጠነኛ ክፍያ በማድረግ እንዲመገቡና ያም ተሰብስቦ መደጎሚያ እንዲሆን ማድረጋቸው ነው፤ይህንን ተግባር በተሳታፊዎቹ ዉይይትና ምርጫ 2 እህቶች ለተከታታይ ሁለት ዓመት ይሾማሉ። *የመጀመሪያውን የምርጫ ስብሰባም ሆነ እንዳስፈላጊነቱና ሲጠየቅ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል።*

10.1 **በዚህ መልክ ለሚደረገው እንቅስቃሴ አባላት በሚቀራረቡበት አማራጭ በቡድን ይዋቀራሉ፤**

10.2 **ለቡድኑ ቢያንስ የቅርብ አሰተባባሪዎችን እራሳቸው መድበው ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው እና ለአሰተባባሪዎች ያሰታውቃሉ ወይም አመቺነቱ ከታመነበት በሥራ አሰከያጅ ኮሚቴው ይመደባሉ፤**

10.3 **በቡድኑ ተራ ጊዜ አባላቱን በከፊል ወይም በሙሉ አሳትፎ የሚጠበቅበትን መስተንግዶ ማቅረብ የቡድኑ ሀላፊነት ይሆናል፤ ይህም ውጤት በየቡድኑ ስም ተመዝግቦ በአሰፈላጊ ወቅትና ከአመቺ መንገድ ለምዕመናን ይገለፃል፤**

10.4 **ምዕመናን በዚህ የሰንበት ምሳ አቅርቦት ቡድን ውስጥ እኔም አንድ ቀን ለማርያም ብለው እንዲደራጁና የቡዱኑን ቁጥር በማበራከት ዞሮ የሚደርስበትን ጊዜ እንዲያራዝሙ በአስተዳደሩ አስፈላጊ ጊዜ እየመረጠ ይነግራል።**

10.5 **በዚህ መልክ የሚቀርበው ምግብ ለአንድ ምሳ** <u>$5.00</u> **ብር ብቻ እንዲከፍሉ ተወስኖአል።**

## 11. <u>**የበዓል ዝግጅት**</u>

**ለቤተክርሰቲያኗ ገቢ ማጎልበቻ ተብለው የሚታቀዱ አንዳንድ እንቅሰቃሴዎች በውስጣቸው ገንዘብን ንብረትንና ያባላትን ተሳትፎ የሚመለከቱ ጉዳዮች አሰቀድመው ተነድፈው በሥራ አሰከያጅ ኮሚቴው ሰብሰባ መፅደቅ ይኖርባቸዋል፤**

11.1 **በእንደዚህ ያሉ አንቅሰቃሴች ከምዕመናን በቀጥታ ገንዘብ የሚሰበሰብ ከሆነ ለዚህ ሁኔታ በተለይ በሚዘጋጅ ደረሰኝ ብቻ ይሆናል ለጠቅላላው ገቢ ግን የቤተክርሰቲያኗ ሕጋዊ ደረሰኝ መቆረጥ አለበት፤**

11.2 **በዚህ መሰል በዓል እንደ ሙዳዬ ምፅዋእትና ስእለተን የመሳሰሉ ከተሰበሰቡ ግን በነዚህ ርእሶች ሰለ ገንዘብ አሰባሰብ ይህ የውስጥ መመሪያ በሚያዘው መሰረት መፈፀም አለበት፤**

## 12. ከሚሸጡ ነገሮች ስለሚገኝ ገቢ

ቤተክርስቲያኗ በልዩ ልዩ ያገኝቻቸውንና ለመደበኛም ሆነ ለልዩ አገልግሎት ከምትጠቀምባቸው በላይ ሆነው የሚገኙትን አላቂና ወቅታዊ መገልገያ እቃዎች የዋጋ ግምት በመስጠት ምእመናን በግዥ እንዲያገኟቸው ታደርጋለች፤ ይህም አሰራር ስርዓት እንዲይዝ ለማድረግ በዚህ የውስጥ ደንብ መሠረት የሚከተለው ተወስኗል፤

12.1 ማንኛውም በስጦታም ሆነ በስእለት ለቤተክርስቲያኗ የሚገባ እቃ ሁሉ በገቢ ከመመዝገቡና እንደእቃው ዓይነት በቤተክርስቲያኗ ውስጥ መገልገያ እንዲሆን አግባብ ባላቸው አካላት ማስተም ለንዋዩ ቅድሳት በደብሩ አለቃ፤ ለሌሎች ቁሳቁሶች በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ሳይወሰን ለሽያጭ አይቀርብም፤ በአዘቦቱ ወይም በበአል ቀን ለሕዝብ የሚሸጡ የቤተክርስቲያን እቃዎችን እንዲሸጡ የሚመደቡ ሰዎች እቃዎቹን ከንብረት ሹሙ ቆጥሮ መረከብና በተሰጠው የዋጋ ተመን መሰረት ሸጠው ገንዘቡን በቅፅ 5 ላይ በማስፈር ለገንዘብ ያዥው ማስረከብ ይኖርባቸዋል፤ ለዚህም አገልግሎት በቤተክርስቲያኑ ውስጥ አንድ ስፍራ ላይ እንደ ካሴትና መጻህፍት ቋሚ ቦታ መደርደሪያ ተዘጋጅቷል፤

12.2. በዚህ በተዘጋጀው መደሪደርያ ውስጥ ገቢው ለምእመናን እይታ የሚጠቅሙትና ወጥተውም የሚሸጡት ሁሉ ከላይ በዝርዝር በተገጸው የአመጣጥ መንገድ ለቤተክርስቲያኗ የደረሱትና በዚያም መልክ እንዲከፋፈሉ የተወሰኑ ብቻ ናቸው።

12.3. ለሽያጭ የሚቀርቡ ቁሳቁሶችን ከንብረት ኃላፊው እየተረከበ በተዘጋጀው ቋሚ ስፍራ በመደርደር ለምእመናን የሚሸጥ አካል ወይም አባል በውል ተለይቶ ይታወቃል ። (ይህ የውስጥ ደንብ በተሻሻለበት ጊዜ ማለትም (13ተኛው)ዙር ቦርድ የአስተዳደር ዘመን እቃዎች በሙሉ ትምህርት ነክ በመሆናቸው ኃላፊው የደብሩ አለቃና የስብከተ ወንጌል ሲሆኑ ይህ አካል የመጤትን መጽሀፍት ወይም ካሴት ካጣሩ በኃላ ለንብረት ሹሙ ያሳውቃሉ።

- ወደፊት በእድገት የተለያዩ እቃዎች በቋሚ መሸጫ ቦታዎች ሲደራጁ አግባብነት ባላቸው አካላት ስር እንደሆኑ ሊደረግ ይችላል

# 13. አስተዳደራዊ ሥራዎች

## አጠቃላይ መርህ

የቤተክርስቲያናችን አርቶዶክሳዊ ሥርዓት፤ የእኛነታችን መታወቂያ አኩሪ ባህል፤ የማህበረ ምዕመናኑ ጉባኤ ያፀደቀው መተዳደሪያ ደንብ፤ እና አስተዳደር ቦርዱ የቀረፀው የውስጥ መመሪያ ለምዕናኑና ለአስተዳደር ቦርድ ግንኙነት መሰረቶች ናቸው፤

በዚህ መርህ በመመርኮዝ አባልት ከመረጧቸው አካላት ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ቀልጣፋና አንድ ወጥ ለማድረግ፤

### 13.1 አመራሩን በሀሳብ ሰለመርዳት

ማንኛውም መደበኛ አባል የቤተክርስቲያኗ አሰተዳደር ቦርዱም ሆነ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ትኩረት ሊደረግት ይገባል ብሎ የሚገምታቸውን አሰተያየት በማንኛውም አመቺ ጊዜና ሰአት ለመረጣቸው አከላት እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል፤ ለዚህም በአያጋጣሚው ሁሉ ማሳሰቢያ እንዲሰጥ ይደረጋል፤

### 13.2 የሀሳብ መሰጫ ሳጥን፤

ከላይ በተራ ቁጥር 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ሀሰባቸውን ዘርዘር አድርገው በፅሁፍ ለማቅረብ ለሚሹ አንዲመች በቤተክርስቲያኗ አማካይ ሰፍራ አንድ የሀሳብ መሰጫ ሳጥን መቀመጥ አለበት፤

ሰለ አጠቃቀሙም በዚህ የውሰጥ መመሪያ የሚከተሉት ስርአቶች እንዲሟሉ ተወሰኗል፤

13.2.1. ማንኛውም አባል ለቤተክርስቲያኗ ዕድገትና ለአስራሩ መሻሻል ሀሳቡን ሲያቀርብ ሙሉ ስሙን አድራሻውንና የሰልክ ቁጥሩን ማሰፈር ይኖርበታል፤

13.2.2. የቤተክርስቲያኗ ሥራ አሰኪያጅ ኮሚቴ በወር 2 ጊዜ ሳጥኑን በመክፈት በውስጡ የተገኙትን ሀሳቦች ተመላክቶ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚሻ ከሆነ ሀሳብ አቅራቢውን በአድራሻው በመደወል ያሟላና እንደነገሩ ውሳኔ ይሰጥበታል፤

13.2.3. የጠያቁው ሙሉ ስምና አድራሻ የሌለባቸው ወይም በሚደረገው የማረጋገጫ ጥሪ የሀሳቡ ባለቤት በመዘገበው ሰልክ ሊገኝ የማይችል ከሆነ የሀሳቡ ይዘት ግንዛቤ ውስጥ ሳይገባ ዋጋ እንደሌለው ተቆጥሮ ይወድቃል፤

### 13.3. የማስታወቂያ ሰሌዳ

ቤተክርስቲያኗ ጥላ ሥር የሚሰበሰቡ ምዕመናን በችግርም ሆነ በደስታ በቅርቡ ተገናኝተው እንዲጠያየቁ፤ እንዲረዳዱ፤ የሚጠቅም ማስታወቂያ ለማኖር፤ ቤተክርስትያናችንን የሚመለከቱ ዜናዎች ከተገኙ ምዕመናን እንዲመለከቷቸው ማእከል ለማፍጠር በቤተክርስቲያኑ አስተዳደር ቢሮዎች አካባቢ እና ወደምግብ አዳራሹ መዳረሻ ኮሪዶር ውስጥ የማስታወቂያ ሰሌዳ ይኖራል፤

ይህን አስመልክቶ በዚህ የውስጥ ደንብ 13.3 የቤተክርስቲያኗ ሥርዓት የምዕመናኑን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አምነት፤ የአባለቱን ስሜት፤ ፍቅርና አንድነት የማይፃረሩ ስለመሆናቸው በቤተክርስቲያኗ አስተዳደር ፅ/በት የታዩና የተረጋገጡ ነገሮች እየተለጠፉ ምዕመናን እንዲጠቀምባቸው የአስተዳደሩ ፅ/በት የቅርብ ከትትል እንዲያደርግ ተወስኗል፤

### 13.4 የመላላኪያ አድራሻ ስለማሳወቅ

የቤተክርስቲያናችን አስተዳደራዊ እንቅስቃሴ የሚመራው በመተዳደሪያ ደንቡና በውስጥ መመሪያው ቢሆንም አንዳንድ አስፈላጊ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ምዕመናን (አባላት) አውቀው አስፈላጊውን ያደርጉ ዘንድ ቀልጠፍና አስተማማኝ ሰንሰለት መፍጠር በማስፈለጉ፤

13.4.1 አባላት ሁሉ ሙሉ የመላላኪያ አድራሻቸውን ከነተለዋጭ የሰልክ ቁጥሮቻቸው ለቤተክርስቲያኑ እንዲያስመዘግቡ ይጠቃሉ፤

13.4.2 ቤተክርስቲያን አዘውትሮ ለመገኘት ያልቻሉ ወይም አንድ ሁሉንም የሚመለከት ጉዳይ በተነገረበት እለት በአጋጣሚ ያልተገኙ ምዕመናን እንደ አስላጊነቱ በሰጡት አድራሻ መሰረት በፓስታ ቤት በኩል እንዲደረርሳቸው ለማድረግ ይቻላል፤

13.4.2 ይህ የውስጥ ደንብ ለ3ኛ ጊዜ ሲሻሻል ደግሞ ምእመናን በዓመት ውስጥ ለቤተክርስቲያናቸው ያደረጉትን አስተዋጽኦ በአሃዝ የሚያሳየጨ ማስረጃ ለታክስ ማስቀነሻ እንዲረዳ በሰጡት አድራሻ እንዲላክላቸው የሚያስችል አቅም እድገት ተደርሶበታል።

## ዘገባ፤ ይዞቱና ስረጭቱ

1. የቤተክርስቲያኑ አስተዳደራዊ እንቅስቃሴ በተለይም የገንዘብና ንብረት አሰባሰብን፤ አያያዝን አጠቃቀምን ባካተተ መልኩ እየተዘገበ፤
   በወር አንድ ጊዜ ለሰራ አስኪያጅ ኮሚቴው
   በ 3 ወር አንድ ጊዜ ለአስተዳደር ቦርዱ
   በዓመት አንድ ጊዜ ለማህበረ ምዕመናኑ ጉባኤ መቅረብ አለበት፤ ለዚህ ጥንቅርም ወጥነት እያንዳንዱ የስራ ክፍል የየራሱን በመሰራት ለዋና ፀሀፊው ያሰረክባል፤

2. ማንኛውም ለአስተዳደር ቦርዱ በኦፊሴል የሚቀርብ የፅሁፍ ዘገባ ሁሉ ለቁጥጥር ኮሚቴው በግልባጭ እንዲደርሰ ያስፈልጋል፤

3. የምዕመናንን ልዩ አሰዋፅኦ የጠየቀ እንቅስቃሴ ተደርጎ ውጤት በተጠናቀረበት ጊዜ ሁሉ ምዕመናን አንድ ወጥ እውቀት እንዲኖራቸው አመቺ መንገድ፤ ጊዜና፤ ሁኔታ እንደተመቻቸ መግለጫ መሰጠት አለበት፤ ይህን መሰሉ መግለጫ መደበኛውን የስብሰባ ጊዜና ሰርአት ላይጠብቅ ይችላል፤

## መጪዎች

ለቤተክርስቲያኗ መደበኛ እንቅስቃሴ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉት መጭዎች እንደ እንቅስቃሴው ስፋትና እንደ አቅማችን ጥንካሬ የሚያድጉ የሚጨምሩና የሚለወጡ ናቸው፤

ዕድገት የሚወሰነው ነገር እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ በተነደፈበት ወቀት የቤተክርስቲያኗ ወጭዎች የሚባሉት፤

1. ለሰብአዊ አገልግሎት ወጭዎች
   - 1.1 ለደብሩ አለቃ ካህን
   - 1.2 ለዲያቆን
   - 1.3 ለጊዜያዊ ሰራተኛ
2. ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች
   - 2.1 ለሞረጌጅ
   - 2.2 ለንብረት ኢንሹራንስ
   - 2.3 ለመብራት
   - 2.4 ለጋዝ
   - 2.5 ለውሀና ለፈሳሽ
   - 2.6 ለቴሌፎን
   - 2.7 ለኪራይ አገልግሎት
     - 2.7.1 ለፖሰታ ሳጥን
     - 2.7.2 ለሴፍ ቦክስ
   - 2.8 ለህንፃ ደህንነትና እንክብካቤ
     - 2.8.1 ለቀላል ጥገና
     - 2.8.2 ለተባይ መቆጣጠሪያ
   - 2.9 ለአሰተዳደራዊ ስራዎች

2.9.1 ለቋሚ የፅህፈት ቤት መሳሪያዎች
2.9.2 ለአላቂ የፅህፈት መሳሪያዎች
2.9.3 ለሰነድ ህትመት

2.10 ለመንፈሳዊ አገልግሎት
2.10.1 ለምስጢራተ ቤተክርስቲያን ማከናወኛ
2.10.2 ለሰርሰተ ቤተክርስቲያን አስፈላጊ ነገሮች ማሟያ
2.10.3 ለማጓጓዣና መስተንግዶ
2.10.4 ለሊቀጳጳሱ ፅ/ቤት አሰራት

3. ህጋዊ ለሆነ ጉዳዮች አማካሪ (ለጠበቃ) የሚከፈል
4. ለልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ፤
(ዝርዝሩ በየጊዜው እየተዘጋጀ የሚፈፀም)

## 5. አጠቃላይ የወጭዎች አፈፃፀም መርህ

5.1 ቀድሞ ለሚታወቅ ማንኛውም አይነት ወጭ በአመት የተሰላ በጀት መያዝ ሰላለበት እያንዳንዱ የስራ ክፍል የሚያስፈልገውን በጀት ነድፎ ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው፤ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ደግሞ ለቦርዱ፤ ቦርዱ ደግሞ ለጉባኤው በየደረጃው በማቅረብ

አሳውቀው ማፀደቅና በበጀቱ መሰረት መሰራት አለባቸው፤

5.2 ከጥቃቅን ድንገተኛ ወጭዎች በሰተቀር ክፍያ ሁሉ በቼክ መሆን አለበት፤

5.3 ማንኛቸውም ክፍያ የወጭ ማዘዣና ደጋፊ ሰነዶች መያያዝ አለባቸው፤

# ከሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤትና ከሊቀጳጳሱ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

የአትላንታ ሰዓሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ለስደተኞች ምዕመናን ልጆቿ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ያልተበረዘውንና ያልተደቀለውን የሐገራቸውን እምነት ወግና ባህል ጠብቀው ሕይወታቸውን ይመሩ ዘንድ አቅም በፈቀደው መሰረት ያልተቆጠበ ጥረት እያደረገች ትገኛለች።

ለዚህም ጥረት ታላቅ አስተዋጽኦ በማድረግ በአባትነት ለዚህም ደረጃ ለመድረስ ሲጠብቁንና ሲያገለግሉን የቆዩት አባታችን ብፁእ አቡነ ያዕቆብ በአምላክ ቸርነትና ፈቃድ ከደብር እልቅና በማለፍ በሊቀጳጳስነት እድገት በመድረስ አሁን የአሜሪካ እስቴቶች ማለትም የጆርጂያና የቴነሲ የበላይ አባት በመሆን የሐገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ በመሆን ተሹመዋል። ይህም እርሳቸው ለዚህ ታላቅ ክብር ደርሰው እኛንም አክብረውናል።

ስለዚህም የሰአሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ካቴድራል በሚቀጥለው መሰረት አባታችንን አክብራ እንድምትይዝ ተወስኗል።

1) በሕገ ደንባችን በምዕራፍ 5 ውስጥ የተጠቀሰውን ልዩ ድንጋጌ በማሻሻል የብፁዕ አቡነ ያዕቆብን ስም በማስገባት የሐገረ ስብከቱን ሊቀ ጵጵስና ሕጋዊ ታደርጋለች፤

2) በሕገ ደንባችን ውስጥ በ ም 3 አንቀጽ 19 ከቁጥር 1 እስከ 6 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለብጹዕ አባታችን የሚከተለውን ተጨማሪ ድጋፍ ታደርጋለች፤

ሀ) መንበረ ጵጵስናው በአትላንታ ሰአሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ካቴድራል ሲሆን ለክብራቸው የሚመጥን ጽ/ቤት ቢሮ ታዘጋጃለች፤

ለ) አሁን እየተደረገ እንዳለው ለክብራቸውና ለኑሮአቸው የሚሆን ከኪራይ ፣ ከውሃ፣ ከመብራት፣ ከጋዝ ክፍያ ነጻ የሆነ መኖሪያ ቤት እንዲኖራቸው ታደርጋለች፣

ሐ) ለኑሮአቸው ድጎማ የሚሆን በወር የተመደበላቸው ገንዘብ ይከፈላቸዋል

መ) በሐገረ ስብከታቸው ስር በአሉት እስቴቶች ያሉ ክርስቲያኖችን በማሰባሰብና ቤተክርስቲያናትን እንዲቋቋምምና የተቋቋሙትንም ለመርዳት ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚረዳ ፈንድ ለጽ/ቤታቸው $2500.00 በጀት እንዲያዝ ታደርጋለች፤ (ይህ የመጀመሪያ ስለሆነ ወደፊት ሁኔታው እየታየ ለውጥ ይደረጋል)

ሠ) ከአንድ ደብር እልቅናነት አልፈው የሐገረ ስብከታቸው ስር ላሉ ሁሉ ጠቅላላ የበላይ አባት እንደመሆናቸው መጠን በሐገረ ስብከታቸው ውስጥ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ቤተክርስቲያኗ ሙሉ ፈቃደኛ ነች ።

ረ) የቤተክርስቲያኑ አስተዳደር የደብሩ እልቅና ሃላፊነት ሲሰጥም ሆነ ተጨማሪ ካህን ቢያስፈልግና ቢያስመጣ በደብዳቤ ለሐገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ ያሳውቃል።የሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ ደብዳቤ ሥርዓተ ኖላዊ ተደርሦ ይሾማል። በደብሩ አለቃና በአስተዳደር መሀከል ችግር ቢፈጠር መተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ከሐገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ ጋር በመመካከር አስተደደሩ እርምጃ ይወስዳል፤ችግሩ በሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስና በአስተዳደሩ መካከል ከሆነ ግን ጉዳዩ ለሲኖዶሱ ተላልፎ የማህበረ ምዕመናኑ ጉባኤና ሲኖዶሱ የሚወክላችው አባላት በጋራ እንዲያዩት ይደረጋል።ሁለቱ የሚሰጡት ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

ሸ) ሐገረ ስብከታቸው በርከት ያሉ ስቴቶችን ያካተተ ቢሆንም በውስጣቸው ያሉት ቤተክርስቲያናት በቁጥርም ሆነ ባላችው ምዕመናን ብዛት ገና ያልተጠናከሩ በመሆናቸው ሀገረ ስብከቱን በፋይናንስ መርዳት እስኪችሉ ድረስ በዓመት ሁለት ጊዜ በስደት ያለው ሲኖዶስ ለሚያደርገው ስብሰባ ለመገኘት የአትላንታ ሰዓሊተ ምህረት ካቴድራል የመጓጓዣ ወጭያቸውን ትሸፍናለች፣

ቀ) ቤተክርስቲያንዋ ከማህበረ ምዓመናን ጋር በዓመት ውስጥ በምታዘጋጀው መደበኛ ስብሰባ ላይ በመገኘት ቡራኬና አባታዊ ምክር ይሰጣሉ።በመንፈሳዊ ረገድ በካቴድራሉ ለሚያገለግሉ ካህናት በደብሩ አለቃ አማካይኝነት መመሪያ ይሰጣሉ።አስፈላጊም ሆኖ ሲያገኙት ሁሉንም በጋራ ሰብስበው ሊያነጋግሩ ይችላሉ።

# ካህናትና አስተዳደር

ይህ የውስጥ ደንብ ለሦስተኛ ጊዜ ሲሻሻል በእድገት የተደረሰባችው ሁኔታዎች ሲገመገሙ የአገላጋይ ካህናትም ቅጥርም መጨመሩና ሰፋ ያለ አገልግሎትም ሊሰጥ መታቀዱ አንዱ መሆኑ ተገለጿል።

በመተዳደሪያ ደንቡ ም 3 አንቀጽ 20 ላይ የተዘረዘረው እንደተጠበቀ ሆኖ

1- የደብሩ አለቃ በካቴድራሉ ለሚያገለግሉ ካህናት ግልጽ የሆነ የግልና የጋራ ኃላፊነታቸውን የሚያሳይ መመሪያ አዘጋጅተው ይሰጧቸዋል፣

2- የቤተክርስቲያኑን አገልግሎት በአንድ ወጥ ግንዛቤ ለማቀላጠፍ እንዲያግዝ እንደአስፈላጊነቱ አስተዳደሩና ካህናቱ የጋራ ስብሰባ ያደርጋሉ፣

3- በካህናቱ መካከል አለመግባባት ቢፈጠር መንፈሳዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከሆነ ከሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ ጋር፣

አስተዳደራዊ በሆኑ ጉዳዮች ማለትም አገልግሎትን በሚመለከት ከሆነ ከአስተዳደሩ ጽ/ቤት ጋር በመሆን እንዲፈታ ይደረጋል

# የካቴድራሉን ሕንፃ እንክብካቤ፣አጠቃቀምና አስተዳደር በተመለከተ

በውስጥ መመሪያው መግቢያ ላይ እንደተገለጸው የካቴድራሉ ህናጣ ለምእመናን ከሚሰጠው አገልግሎቶች አንዱ ለማትበራዊ ጉዳዮችም ጭምር እንደመሆኑ እራሱን የቻለ

ሀ - የአጠቃቀምና እንክብካቤ መመሪያ ይኖረዋል

ለ - ለአገልግሎቱ የሚከፈለውም በዝርዝር ይገለጻል

ሐ - እንደ እድገቱ ታይቶ ተጠሪነቱ ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የሚሆን አስተዳደር ይኖረዋል

# ትውልድን የማስተማርና የመተካት ጥረት በተመለከተ

መንደርደሪያ

-ዓላማው
-የአስተዳደሩ ኃላፊነት
-የኮሚቴው አፈጣጠር
-ተቀጣሪ መምህራንና የወላጆች ኃላፊነት በተመለከተ
-በበጀት ረገድ
-በውጤት ግምገማ ረገድ